**በአገራችን ብሔራዊ ክብር አንደራደርም**

**ከኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ**

**ግንቦት 25/2013 ዓ.ም.**

የአገራችን ኢትዮጵያ የረዥም ጊዜ ታሪኳ ከቀይ ባህርና ከአባይ ወንዝ ጋር የተሳሰረ ነው። በመሆኑም ከጥንት ጀምሮ ለህልውናዋ ብቻ ሳይሆን ለሰላሟም ጠንቅ እንደሆነ እስካሁን ቀጥሏል። ቀይ ባህር ማለት ከፍተኛው የምዕራብ አገሮች ንግድ የሚንቀሳቀስበት መስመር በመሆኑ ለአካባቢው አገሮች በተለይም ለኢትዮጵያ ሁልጊዜ የሥጋት ምንጭ ነው። የአባይ ወንዝም እንዲሁ። በመሆኑም ከዚህ በፊት በአገራችን ላይ ከውጭ የተሰነዘሩ ጥቃቶችና ዛቻዎች በቀይ ባህርና በአባይ በኩል መሆናቸው ከታሪካችን ጋር ተያያዥነት አላቸው።

የአፍሪቃ ቀንድ ስትራቴጂክ አገር ተብላ በምትጠራው ጎረቤታችን ጅቡቲ ውስጥ ከዘጠኝ አገሮች በላይ የጦር ሠፈር መሥርተው ኢትዮጵያንና የአፍሪቃ ቀንድ አገሮችን በዓይናቸው ሥር አድርገው ይመለከታሉ። በአፍሪቃ ቀንድ አካባቢ የአፍሪቃ ምሰሶ ተብላ በምትጠራው ኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ጥቅም ያላቸው መሆኑን አመላካች ነው። በአሁኑ ሰዓት በውጭ ኃይሎች በተለይም በአሜሪካ በልዩ ልዩ ሽፋኖች፣ በሰብዓዊነትና በዴሞክራሲያዊነት ሽፋን እየተቀነባበረ ብሔራዊ ደህንነታችንን አደጋ ላይ የሚጥል እርምጃ እየተወሰደ ያለው ሀገራችን ካለችበት ቀጠና የፖለቲካና ጂኦግራፊያዊ ዳራ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ግልጽ ነው።

ኢትዮጵያ ቀደም ብሎ የነበረባት ጫና አብዛኛውን ጊዜ ከሩቅና ከቅርብ ጎረቤቶቻችን የሚነሳ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ግን አገራችን በውስጣዊና በውጫዊ ጠላት ተሰንጋ የተያዘችበት ወቅት ስለሆነ ብሔራዊ ክብራችንን እና ደህንነታችንን የሚፈታተንበት ጊዜ ሆኗል።

በህወሓት መሩ አገዛዝ ለረዥም ዓመታት የተዘራው የዘረኝነትና የጥላቻ መርዝ ፍሬ አፍርቶ ሕዝባችንን እርስ በርስ እያተራመሰ ለውጭ ጠላት መግቢያ በር ከፍቶብናል። ትግራይ ውስጥ በነበረው የአገር መከላከያ ሠራዊት ላይ አሸበሪው የህወሓት ቡድን ጦርነት ከከፈተበት ቀን ጀምሮ ብዙ ወገኖቻችን የሕይወት ዋጋ ከፍለዋል፣ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፣ ለከፍተኛ ችግርም ተዳርገዋል። በዚህ አስከፊ ጦርነት ውስጥ ከዚህም በላይ የገዘፉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተፈጽመው ሊሆን እንደሚችል የጦርነትን አጥፊነት የሚገነዘቡ ሁሉ ያውቁታል። ይህን በተመለከተ ኢሕአፓ በወቅቱ ባወጣው መግለጫ የተሰማውን ሀዘንና ለሕዝባችን ያለንን ወገንተኛነታችንን ከመግለጻችን በተጨማሪ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖቻችን ሁሉ በቂ እርዳታ እንዲደርሳቸው፣ የተበደሉ ፍታኀዊነትን እንዲጎናጸፉ፣ ወንጀል የፈጸሙትን ወደ ሕግ በማቅረብ አስፈላጊውን ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስቧል። አሁንም ይህን አቋማችን በድጋሜ እየገለጽን የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጲያዊ ወገናችን ነውና ጉዳቱ፣ ሰቃዩና እንግልቱ እኛንም የሚያመን መሆኑን አበክረን መግለጽ እንወዳለን።

ይሁን እንጂ የአሜሪካ መንግሥት ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም በመሬት ላይ ያለውን እውነታ ባላገናዘበ፣ በዕውቀትና በመረጃ ላይ ባልተመሠረተ ወደ አንድ ወገን ያጋደለና የሃሰት ዘገባ ለዓለም ኅብረተሰብ በማሰራጭት በአገራችን ላይ ፖለቲካዊም ሆነ የኢኮኖሚ ጫና ለመፍጠርና ኢትዮጵያን በመዳፉ ሥር ለማስገባት ከፍተኛ ግፊት እያደረገ ነው።

የአሜሪካ ዘገባ አድሏዊ ነው የምንለው ትግራይ ውስጥ ተፈጸመ የተባለውን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት እነሱ በሚፈልጉትና ይጠቅመናል ባሉት መልክ አቀነባብረው ለምክር ቤታቸው ሲያቀርቡ ሁመራ፣ ወልቃይት፣ ማይካድራና ሌሎችም ቦታዎች ላይ የህወሓት ነብሰ ገዳይ ቡድን (ሳምሪ) የፈጸመውን ኢ-ሰብዓዊ ግድያ አንድም ቦታ አለመጠቀሱ አንድ ማሳያ ነው።

ይህ ጭፍጨፋ በአምንስቲ ኢንተርናሽናልና በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት አስጠባቂ ድርጅት በማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ አሜሪካ ግን ይህን አታነሳም።  እንዲሁም አገር ሰላም ነው ብሎ በተኛው በአገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት ላይ አሸባሪው ህወሓት ያደረሰውን ኢ-ሰብዓዊ ጭፍጨፋ እንኳን በዘገባው ውስጥ ለማጠቃለል ቀርቶ በጭራሽ መስማትም አይፈልጉም።  ሣራ ቻርሊስ የተባሉት የአሜሪካ የእርዳታ ሰጭ ድርጅት ኃላፊ ለአሜሪካ የምክር ቤት አባላት በሰጡት ምስክርነት የረሀቡንና የመፈናቀሉን መጠን ምን ያህል ከፍ ያለ እንድሆነ ይጠቅሳሉ።  ሆኖም ግን ከጦርነቱ በፊት የትግራይ ሕዝብ የነበረበትን የኑሮ ሁኔታ ማለትም ከሁለት ሚሊዮን በላይ በስንዴ ምጽዋት ይኖር እንደነበር እየታወቀ በአጠቃላይ አሁን ያለውን ችግር ሙሉ በሙሉ በጦርነቱ የተከሰተ አድርገው ማቅረባቸው ሚዘናዊነት የጎደለው ነው።

በቤንሻንጉል ጉሙዝና በወለጋ ለረጅም ጊዜ የተፈጸሙት የጭካኔ ተግባራት እንዲሁም በቅርብ ጊዜ በአጣዬ፣ በሸዋሮቢት እና ካራቆሬ የተፈጸሙት ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶች ከምንም ሳይቆጠሩ አሜሪካ በቁስላችን ላይ ጨው በመነስነስ በኢትዮጵያ የተወካዮች ምክር ቤት በአሸባሪነት ከተፈረጀውና በጦር ሜዳ ከተሸነፈው የህወሓት ቅሪት ጋር መንግሥት ቁጭ ብሎ እንዲደራደር ጥሪ ማቅረቧ የሚያስገርምም  የሚያሳዝንም ነው።  በተጨማሪም በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብቶ በሀገራችን ፖሊስ ኃይሎች ስምሪት ላይ ትዕዛዝ ለመስጠት መሞከሩ እጅግ አሳዛኝና በሀገራችን ውስጥ ግጭትን ይበልጥ የሚጋብዝ አደገኛ አቋም ሆኖ አግኝተነዋል።

በአንድ በኩል አሸባሪነትን እዋጋለሁ የምትለው አሜሪካ ከአሸባሪ ጋር ተደራደሩ ማለት ምን  ማለት ነው? በአሜሪካ ውስጥ ኮንፌደሬቶች ከፈደራሊስቶች ጋር በተለዩበት ጊዜ በ1861 ዓ ም (እአአ)፣ በጃፈርሰን ደቪስ የሚመራው የኮንፈድሬቶች ጦር ፖርት ሰመር ላይ በነበረው የአገሪቱ መከላከያ ኃይል ላይ አደጋ ጥለው በመጨፍጨፋቸው የእርስ በርስ ጦርነቱ በይፋ ተጀመረ። በሁለቱም በኩል ብዙ ሕዝብ አለቀ፣ ንብረትም ወደመ።  ይህ ለአራት ዓመት የዘለቀው የእርስ በርስ ጦርነት ሲደረግ ተኩስ ይቁምና በሰላማዊ መንገድ ድርድር ይደረግ በተባለበት ጊዜ ፕሬዘዳንት አብርሃም ሊንከን የአገሪቱን መከላከያ ኃይል ከጨፈጨፈ ጋር አልደራደርም በማለት ጦርነቱን ቀጥለው የኮንፌድሬቶች ጦር ተሸንፎ ጦርነቱ ተደመደመ።  ይህን ዓይነት ታሪክ ያላት አሜሪካ ተቸንፎ ከተበተነ የሽፍታ ቡድን ጋር ተደራደሩ ማለት እንዴት ይቻላታል?  ፕሬዘዳንት አብራሃም ሊንከን እንዳሉት እኛም ለአገራችን ብሔራዊ ክብር አለን።

ስለዚህ በተሳሳተና በአድሏዊነት በተሞላ ዘገባ ላይ በመመርኮዝ በአገራችን ላይ አሜሪካ የጣለችውን ማዕቀብ አጥብቀን የምንቃወም መሆናችንን በማያወላዳ ቋንቋ ለመግለጽ እንወዳለን፡፡ የአገርን ብሔራዊ ጥቅምና ክብርን ለማስጠበቅ የድርጅት ጉዳያችን ይቀድማል ብለን እጃችንን አጣጥፈን የማንቀመጥ መሆኑንና ከሕዝባችን ጎን በመቆም የሚፈለገውን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆናችንን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስንገልጽ በታላቅ ሀገራዊ ኩራት ነው፡፡

ሌላው በብሔራዊ ክብራችን ላይ የተጋረጠው አደጋ ግብፅና ሱዳን በታላቁ ህዳሴ ግድባችን ምክንያት ለዓመታት የዘለቀ ሤራ እየፈጸሙብን መሆኑ ነው፡፡ በአገራችን ውስጥ የተፈጠረውን የውስጥ ችግር ምክንያት በማድረግ ሱዳኖች ጦር ሰብቀው በምዕራቡ የአገራችን ክፍል ድንበር ጥሰው መሬታችንን ይዘው ከግብጽ ጋር የወረራ ፍላጎትን አመላካች የሆነ የጋራ ወታደራዊ ሥልጠና እያደረጉ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡ አሜሪካ የኢትዮጵያን ጥቅም በማያስጠብቅ መልኩ ችግሩ እንዲፈታ በኢትዮጵያ ላይ ጫና እያደረገች እንደሆነ የተለያዩ የዜና አውታሮች ካቀረቡት ዜና ተረድተናል፡፡ ይህም የአሜሪካ ወገንተኝነት ወዴት እንደሆን በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከሠላሳ ዓመት በላይ የተዘራው የዘውጌ ዘር አድጎ የአገራችን የሕዝባችንን ሰላም እየነሳ ባለበት ሁኔታ ግብፅና ሱዳን አገር አፍራሽ የሆኑትን ኃይሎች በማሠልጠን፣ በማስታጠቅና በገንዘብ በመርዳት ሰላማችንን እንድናጣ የተቻላቸውን ሁሉ እያደረጉ ነው፡፡

ስለዚህ ጊዜው አገራችን በውስጥና በውጭ ጠላቶች ተወጥራና ተከባ የተያዘችበት ወቅት ስለሆነና ጉዳዩ ከፖለቲካ ድርጅት እምነት በላይ በመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ለአገራችን ብሔራዊ ክብር ሊከፈል የሚገባውን ዋጋ ሁሉ ለመክፈል ዝግጁ መሆኑን ለሕዝባችን ሁሉም በአጽንኦት ይገልጻል፡፡

አገር እንዲህ ባለ የውስጥና የውጭ አስከፊ ሁኔታ ላይ በወደቀችበት ወቅት፣

1. የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት ቆሞ ብሔራዊ አንድነቱንና ክብሩን እንዲያስጠበቅ ኢሕአፓ ጥሪውን ያቀርባል፡፡ አሜሪካ በአገራችን ላይ የጣለችውን ማዕቀብ በመቃወም በጋራ ጠንካራ ድምፃችንን ማሰማት ይኖርብናል፡፡
2. ተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ ውስጣዊ ልዩነቶቻችንን ወደጎን በመተው እና በአንድነት በመቆም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመሆን አገራችንን እንድንታደግ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡
3. መንግሥት ከፍተኛ አገራዊ ሃላፊነት እንዳለበት ባለመዘንጋት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ ላይ ሆኖ ብሔራዊ ክብሩን እዲያስጠብቅ ጥሪ እንዲያደርግ ኢሕአፓ ያሳስባል፡፡
4. መንግሥት የውጭ ዲፕሎማሲያዊ ሥራውን አጠናክሮ እንዲቀጥል እናሳስባለን፡፡

5. ከውጭ ኃይላት ጋር እየተላላኩ በአገር ውስጥ ሕዝባችንን በመግደልና በማፈናቀል ሰላም የሚነሱ አሸባሪዎች ላይ የሚደረገው ሕግ የማስከበርና ሰላምና መረጋጋትን ለማምጣት የሚወሰደው እርምጃ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እናሳስባለን።

6. በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል በተፈጠረው የውስጥ ችግር ምክንያት ቤተሰባቸውን ላጡ፣ ከቦታቸው ለተፈናቀሉና ቤት ንብረታቸውን ላጡ ሁሉ የሚደረገው ሰብዓዊ  እርዳታ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እያሳሰብን ኢሕአፓም የበኩሉን አስተዋጽዖ እንደሚያድርግ እናረጋግጣለን።

7. የህዳሴው ግድብ ሁለተኛው ዙር የውሃ ሙሌት በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ እንዲጠናቀቅ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ድጋፋችንን አጠናክረን እንድንቀጥል ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ኢትዮጵያ በቆራጥ ልጆቿ ታፍራና ተከብራ ትኖራለች !

የኢትዮጵያ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)